ፓኖራማ ቁጥር 77

የትዝብት አድማስ

መስከረም 3 2002 ዓም

## ኮሌራ ሰው ፈጀ

የዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት ሰሞኑን ባወጣው ዘገባ መሠረት በኢትዮጵያ የኮሌራ ወረርሽኝ በሽታ በከፍተኛ ፍጥነት ሰውን እየፈጀ መሆኑ ተገልጿል ። በተለየም ደግሞ በአዲስ አበባና በአካባቢዋ በሚኖሩ ዜጎች ላይ በሽታው እየተዛመተ በመሆኑ ፥ ከቁጥጥር ውጭ እየሄደ ለብዙ ሰው ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል ። የሕዝብ ጤና ጥበቃ ባለሙያዎች እንደ ሚገልጹት ፥ የኮሌራ በሽታ መንስዔው በአመዛኙ የፅዳት ጉድለት ፤ የንፁህ መጠጥ ውሀ አለመኖርና የአካባቢ ብክለት እንደሆነ ይነገራል። የአዲስ አበባ ከተማ አቀማመጥ ከምድር ወለል ከፍታ በላይ ስለሆነ፥አየሯ ነፋሻና ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ጤና ተስማሚ እንደሆነች ሁሉም የሚያውቀው፥በተለይም የሀገር ጎብኝዎችን ቀልብ የሚስብ አካባቢ መሆኑ ተደጋግሞ የሚነገር ሀቅ ነበር ። ዛሬ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥሩ በበርካታ ሚሊዮን የሚገመት እንደሆነም ሁሉም ሰው የሚያወራው ጉዳይ መሆኑ ከታወቀ ዓመታት ተቆጥረዋል ። የነዋሪዋ ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ ቢሄድም ለሰው ልጅ መሠረታዊ አገልግሎቶች የሚሆኑ ነገሮች ተሟልተው ሊቀርቡ አልቻሉም ። የውሃና ፈሳሽ አገልግሎቶች እጅግ ሲበዛ ኋላ ቀር ከመሆናቸው አልፈው ተርፈው፥ የሁሉንም ነዋሪዎች ፍላጎት ሊያሟሉ አለሆነላቸውም ። የውሀ እጥረት ሕዝብን እያስቸገረና እያሰቃየ ነው። ይህም በመሆኑ፥ በአብዛኛው የከተማይቱ ክፍል ያለው አየር ጠረኑ እጅግ የሚከረፋና ለሰው ልጅ ጤና ጠንቅና መርዛማ ሆኗል ። በአብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማዎች የሚዘዋወረው ሰው አፍንጫውን ሸፍኖ ሲሄድ ማየት የተለመደ ትዕይንት ብቻ ሳይሆን፥ወደ አዲስ ባኅል የተሸጋገረ መሆኑንም ብዙ ተመልካቾች ደጋግመው የሚገልፁት ጉዳይ ሆኗል ። በጠቅላላውም የከተማይቱ የአየር ንብረት ከተበከለ በርከትከት ያሉ ዓመታት አልፈዋል ። የቆሻሻው በየቦታው መቆለሉ የከተማይቱን ውበት ከማፀየፉ አልፎ ተርፎ፥ የከተማዋን ስም ከአዲስ አበባነት ወደ አዲስ ጥምብነት እየለወጣት ይገኛል።

“ አንች አዲስ አበባ ጣፋጭ ማዓዛሽ

ጠረንሽ ወለላ ከዕንቅልፍ ቀስቃሽ ” ፥

እንዳልተባለላት ሁሉ ፥ ዛሬ ደግሞ

“ መኖር ዕንቆቅልሽ ሕይወት እንቆቅልሽ፥

ዕጌረዳ አበባ እንዳልቀሰምኩብሽ፥

የኔይቱ አዲስአባ ከረፋ ጠረንሽ ። ”

እየተባለ የሚታዘንላት ከተማ ሆናለች፥ አዲስ አባ !

ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላት አዲስ አበባ ከተቆረቀረችበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ውጣ ውረዶች የተፈራረቁባት ከተማ መሆኗ ባይዘነጋም፥ በሕይወቷ ነዋሪዎቿን እንዲህ እንደ ዛሬ ያለ መከራና ችግር ሲገጥማቸው እንዳላየች ታሪኳ ይመስክርላታል። በዕርግጥ መጀመሪያ ስትመሰረት በዘመናዊ የከተማ መሠረተ- ዕቅድ/ ማስተር ፕላን ላይ የተቆረቆረች ባለመሆኗ ፥ ለነዋሪዎቿ መሠረታዊ ፍላጎት የሆኑት አቅርቦቶች በሚመቸው መንገድ ለማሟላት እንዳልቻለች የታወቀ ነው ። ይህ ድክመት ደግሞ የአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛዎቹ በሦስተኛ ዓለም በሚባሉ ሀገሮች በሚገኙ ከተሞችም ጭምር የሚንፀባረቅ ነው ። ይህ ሀቅ እንዳለ ሆኖ ግን ፥ በየጊዜው ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ የሚመጣውን የነዋሪዎቿን ብዛት ለማስተናገድ የሚያስችላት አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከበዳት የሚመጣ በመሆኑ መሠረታዊ የሆኑትን የነዋሪዎቿን ፍላጎት ለማሟላት አልቻለችም ። የኮሌራ በሽታ ዓይነተኛ ምክንያቶች የሆኑትን ለማጥፋት ቀርቶ ለመከላከል አልሆነላትም ። የወገን ባዕዳን የሆኑት ወያኔዎችም ለችግሯ መፍትሄ መፈለጋቸው ቀርቶ ፤ እንዲያውም ይባስ ብለው የመከራዋ ሰበብና ምክንያቶች ሆነዋል ። የኮሬላ በሽታ ዋናው ምክንያቱ የፅዳት ጉድለት መሆኑ እየታወቀ ፥ ፅዳትን ለመጠበቅና አካባቢንም ከብክለት ለመከላከል ፍላጎቱም፥ችሎታውም ይሁን ዝግጁነቱ የላቸውም ። ለነገሩማ ለራሷ ለሀገሪቱ የቆሙ እንዳልሆኑ እየታወቀ ፥ለከተማዋ ያስባሉ ተብለው የሚጠበቁ አይሆኑም።ያማ ባይሆን ኖሮ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው የነዋሪዎችን ጤና መጠበቅ በሆነ ነበር ። በኢትዮጲያ የኮሬላ ወረርሽኝ መቅሰፍት መስፋፋት፥ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት የሰሞኑ ከፍተኛ አሳሳቢ ጎዳይ ቢሆንም ፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአብዛኛው የዓለም ሀገሮች ዘንድ ሊጠፉ የቻሉት ሌሎች ልዩ ልዩ በሽታዎችና ተውሳኮች የሚገኙባት ሀገር ነች። ሌላው ቢቀር ቀደም ባሉት ጊዚያት የንዳድ-ወባ በሽታ መፈልፈያ የነበሩት የወባ ትንኞች በአብዛኛው ጠፍተው እንደነበር ፥ በወቅቱ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር ተቋቁሞ የነበረው የወባ ማጥፊያ ድርጅት ሲያከናውነው የነበርው ተግባር ታሪካዊ ምስክር ነው ። ዛሬ በወባ በሽታ

የሚረግፈውን ኢትዮጵያዊ ቁጥር በትክክል ለማወቅ የሚቻል እንዳልሆነ ሀገር ወዳድ የሆኑት የኢትዮጵያ የጤና ባለሙያዎች በሀዘን ይገልፁታል ። ከዚህም በቀር በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖረው ዜጋ ፥ በኩፍኝ ፥ በአንገት አደንዛዥ (መነጃይትስ) በሽታ፥ በእንቅርት፥ በቆላ ቁስል ፥ በባላዘር በሽታ ፥ በብልሀርዝያ ፥ በኤች አይ ቪ ኤይድስ ልክፍት፥ ወዘተ እንደ ቅጠል የሚረግፍ ለመሆኑ ለማንም የተሰወረ ሊሆን አይችልም ። እነዚህን በሽታዎች ከተቻለ ለማጥፋት ፥ ያ ቢቀር ደግሞ ለመከላከል የሚቻልበትን ዕቅድ ማውጣት ሲቻል ፥ ይህ እየተደረገ አይደለም። ሀገሪቱ በስንት ችግር ያሰለጠነቻቸው የህክምና ዶክተሮች ፥ ነርሶች ፥ ሌሎች የህክምና ባለሙያዎችና ሠራቶኞች የሀገራቸውን ህሙማን ለመርዳት የሚያስችላቸው ዕድል እየተዘጋባቸው ፥ በብዛት እየተሰደዱ ማየት የተለመደ ሆኗል ። የሚያሳዝነው ደግሞ ፥ ምዕራቡ ዓለም የህክምና ባለሙያዎች ዕጥረት እንዳለው ሁሉ ፥ የኢትዮጵያ የጤና ባለሙያዎች ለመገልገል የሚሰደዱት ፥ የአውሮፓንና የሰሜን አሜርካን ሆስፒታሎችንና የጤና ተቋማትን ሆኗል ። ይህ የኢትዮጵያ የጤና ባሉያዎች መሰደድ፥ ከጠቅላላው የሀገረቱ የሠለጠነ ኃይል ፍለስት ጋር የተዛመደ በመሆኑ ፥ ይህ ዘረኛ የወያኔ ሥርዓት በሥልጣን እስካለ ድረስ አሳዛኙ ክስተት በከፋ መልኩ መቀጠሉ አይቀርም ። ለህገርና ለሕዝብ የሚቆሙ ሥርዓትና መንግሥት እስከሚመጡ ድረስም ኢትዮጵያ ሀገራችን በጤናው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በሁለንተናዊው ገፅታዋም እየከሰመች፥ ዜጎቿም እየተጎዱ መሄዳቸው የማይቀር ነው ። የኢትዮጵያን መክሰምና የዜጎቿንም መጎዳት አበክሮ የሚፈልገው ወያኔም፥ለሀገሪቱና ለዜጎቿ ይህን የመሰለ ፤ ዕጣ -ፈንታ ሲገጥማቸው ፥ ኋይላ ( ጮቤ ) እንደሚደነክር ያለፈ ታሪኩ አርጋግጦለታል ።

የኢትዮጵያ ዋና መዲና ብቻ ሳትሆን ፥ የዓለም አቀፍ መናሃርያ የሆነችው አዲስ አበባና አካባቢዋ ፥ በኮሌራ በሽታ መበክል ቢገለፅም፥ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች በዚህ ወረርሽኝ በሽታ ምን ያህሉ እንደተለከፉ በትክክል ሊታወቅ አልተቻለም ። እንኳን ዛሬ በዘር መስተዳደር በተከፋፈለችው ኢትዮጵያ ቀርቶ ፥ ቀደም ሲልም ቢሆን የኢትዮጵያ አምባገነን ገዥዎች የሀገሪቱን ረሀብና ጠኔ፥ በሽታና ችግር ዓለም እንዳያውቀው ይሰውሩት እንደ ነበር የቅርብ ትዝታ ነው። የአዲስ አበባና የአካባቢዋ ነዋሪዎች በኮሌራ በሽታ ምክንያት አደጋ ላይ በመውደቃቸው ምክንያት ምናልባት የዓለም አቀፍን ትኩረት በማግኘት አስቸኳይ ርዳታ ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል ። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች ግን እንኳንስ አስቸኳይ ርዳታ ሊያገኙ ቀርቶ ፥ በበሽታው ምክንያት ምን ያህል አደጋ እንደሚያንዣብባቸው እንኳ ብትክከል ለመታወቅ አይቻልም። የወያኔ ግለሰቦች የቅድሚያ ዕቅድ፥ እንወክለዋለን ለሚሉት አካባቢ መሆኑን ከእነርሱ በቀር ማንም ሊያውቀው የሚችል ባይኖርም፥ ለቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ልባቸው ራርቶ በበሽታ ለሚረግፈው ዜጋ አስቸኳይ የህክምና ርዳታ ለማድረግ ጊዜው ይኖራቸዋል ተብሎ አይጠበቅም። ገና በጫካ ሳሉ ጀምሮ ለርሃብተኛው

ሕዝብ ተብሎ ከውጭ የሚመጣውን እህልም ሆነ መድሃኒት ለራሳቸው ድርጅት ጥቅም ሲያውሉት እንደነበረ ድፍን አገሩ አውቆ መዝግቦታል ። በትግል ስም ስንት ዓይነት ወንጀሎች ሲፈፅሙ እንደነበረ ፣ ሌላው ቀርቶ፣ከእነርሱ ጋር አብረዋቸው ሲታገሉ የነበሩት አሁን ከወያኔ ድርጅት የወጡ የራሳቸው ሰዎች በማስረጃ በተደገፈ ጽሁፎች እያጋለጧቸው ይገኛሉ ።

ሁሉም ዜጋ በትክክል እንደሚረዳው ፣ የሀገራችን የኢትዮጵያ ችግሮችና አደጋዎች፣ ዘርፈ-ብዙና የተወሳሰቡ በመሆናቸው ፣ አንዱን አንስተን ሌላውን ልንተወው የሚቻለን አይሆንም ። ምንም እንኳን የኮሌራው ወረርሽ ያስከተለውን መቅሰፍት ለመከላከል የሀገር ቤትና የዓለም አቀፍ ጥረትና ርብርቦሽ እንደሚያስፈልገው እየጮኽን ብናሳስብም ፣ በተለያየ መልክ በየጊዜው እንደ መንጥር ዕሳት የሚፈራረቁትን አደጋዎች በመካላከል ብቻ ዘላቂ ችግሮቻችንን ማስወገድ ከቶ አንችልም ። ለዘላቂ ችግሮቻችን ዘለቄታ መፍትሔ ፈልጎ የማግኘቱ ጉዳይ የሚያከራክር አይሆንም ። መሠረታዊ ችግሮቻችንን ለማስወገድ፣ በግድ የሦስት ኃይሎችን ትብብርና ቅንጅት ማግኘት ይኖርብናል ። እነርሱም የመጀመሪያው ያው ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን ፣ሁለተኛዎቹ ደግሞ ልዩ ልዩ ሕዝባዊ ተቋማትና ድርጅቶች ሊሆኑ ይገባል ። በሦስተኛ ደረጃ የሚመጣው ደግሞ ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ የተመረጠ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ነው ። ይህ እስካልተሳካ ድረስ ፣ ኢትዮጵያ ሀገራችን፣ ስለጤና ፣ ትምህርት ፣ ስለ ሀገር ልማትና የሕዝብ ብልፅግና፣ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ የወደፊት ርምጃ ማሰብ ኅልም ነው ። ለኢትዮጵያ የቆመ መንግሥት ለማምጣት ፣ በግድ ለኢትዮጵያ ያልቆመውን ወያኔን ፣ ከነዘረኛ ሥርዓቱ ማስወገድ ይዋል ይደር የሚባል ተግባር አይደለም ። የወያኔ አገዛዝ ዋናው ወረርሽኝና ኮሌራ በመሆኑ በጋራ ትግል እናጥፋው !